የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፷
አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፩ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

18th Year No. 60
ADDIS ABABA 27th August, 2012

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯፻፷፯/፪ሺ፬ ዓ.ም

**የጫት ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ……….ገጽ ፮ሺ፭፻፵፫**

CONTENTS

**Proclamation No. 767/2012**

Chat Excise Tax Proclamation ……. Page 6543

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፷፯/፪ሺ፬

## ስለጫት ኤክሳይዝ ታክስ የወጣ አዋጅ

የአገር ውስጥ የጫት ፍጆታ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ በመሄዱ ይህንን ሁኔታ ለመለወጥ የሚያግዝ የታክስ ስርዓት ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በጫት ላይ የሚከፈለውን ታክስ አሰባሰብ ፍትሐዊነት ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የጫት ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር ፯፻፷፯/፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "ታክስ" ማለት በኢትዮጵያ በሚካሄድ የጫት ግብይት ላይ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከፈል የኤክሳይዝ ታክስ ነው፤

፪/ "ታክስ ከፋይ" ማለት የጫት ኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ ነው፤

## PROCLAMATION No. 767/2012.

## A PROCLAMATION ON CHAT EXCISE TAX

WHEREAS, it has become necessary to introduce a tax system that helps to reduce the domestic consumption of chat which is growing at higher rate;

WHEREAS, it is necessary to ensure equity in the collection of the tax payable on chat;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (11) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Chat Excise Tax Proclamation No.767/2012".

**2. Definitions**

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1) "tax" means the excise tax payable on chat transaction in Ethiopia in accordance with this Proclamation ;

2) "tax payer" means a person liable to pay chat excise tax;

፫/ “የታክስ ባለስልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ነው፤

፬/ “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ቢሆንም ባይሆንም ማንኛውም ድርጅት ነው፤

፭/ “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕ□መንግሥት አንቀጽ ፵፯ የተመለከተው ማንኛ□ም □ልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፮/ “ሚኒስቴር” ማለት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ነው፡፡

## ፫. <u>ታክስ የመክፈል ግዴታ</u>

ጫትን በይዞታው ስር በማድረግ፣ በማጓጓዝ ወይም በማንኛውም መንገድ ለሽያጭ የሚያቀርብ ሰው በዚህ አዋጅ የተወሰነውን ታክስ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

## ፬. <u>የታክሱ ማስከፈያ ልክ</u>

በአገር ውስጥ ተመርቶ በመነሻው ክልል ጥቅም ላይ የሚውልና ወደሌላ ክልል የሚጓጓዝ ጫት በኪሎ ግራም ብር ፭ /አምስት ብር/ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልበታል፡፡

## ፭. <u>የታክሱ ማስከፈያ ቦታ</u>

በዚህ አዋጅ በጫት ላይ የተጣለው ታክስ የሚሰበሰበው የታክስ ባለሥልጣኑ አግባብነት ካላቸው ክልሎች ጋር በመመካከር በሚወስናቸው ቦታዎች ይሆናል፡፡

## ፮. <u>ታክሱን የመሰብሰብ ኃላፊነት</u>

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት በጫት ላይ የተጣለውን ታክስ የሚሰበስበው የታክስ ባለስልጣኑ ይሆናል፡፡

፪/ የታክስ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት ከጫት ላይ የሰበሰበውን ታክስ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በተደነገገው መሠረት የገቢው ባለቤት ለሆኑ ክልሎች በየወሩ ያከፋፍላል፡፡

## ፯. <u>ለውጭ ገበያ ስለሚቀርብ ጫት</u>

፩/ በውጭ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ላኪዎች፡-

ሀ) ለውጭ ገበያ በሚያቀርቡት ጫት ላይ ሊከፈል ለሚገባው ታክስ ክፍያ የሚውል ቫውቸር በታክስ ባለስልጣኑ ይሰጣቸዋል፤



3) “Tax Authority” means the Ethiopian Revenues and Customs Authority;

4) “person” means a natural person or an organization whether it is juridical person or not;

5) “region” means any state referred to under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

6) “Ministry” means the Ministry of Finance and Economic Development.

## 3. <u>Duty to Pay Tax</u>

Any person who possessing, carrying or otherwise handling chat for sale or destined for sale shall be liable to pay the tax levied under this Proclamation.

## 4. <u>Rate of the Tax</u>

Chat locally produced and to be supplied for sale or destined for sale shall be charged at a tax rate of Birr 5 (Five Birr) per kilogram.

## 5. <u>Place of Collection of the Tax</u>

The place of collection of the tax levied in accordance with this Proclamation shall be determined by the Tax Authority in consultation with the concerned regions.

## 6. <u>Power to Collect Tax</u>

1/ The tax levied under this Proclamation shall be collected by the Tax Authority.

2/ The tax collected in accordance with this Proclamation shall be distributed by the Tax Authority, on a monthly basis, to the regions to which such revenue is assigned by the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

## 7. <u>Chat Supplied to a Foreign Market</u>

1/ The exporters of chat:

a) shall be issued a voucher book by the Tax Authority to enable them to pay the tax levied on chat under this Proclamation;

ለ) ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡትን ጫት በአገር ውስጥ በሚያጓጉዙበት ጊዜ በጫቱ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ቫውቸር በታክሱ ማስከፈያ ቦታ ለተመደበው የታክስ ባለስልጣኑ ሠራተኛ ያስረክባሉ፤

ሐ) የቀረጥና ታክሱ ሂሳብ በቫውቸር የተከፈለበትን ጫት ለውጭ ገበያ በማቅረብ ቫውቸሩን በየወሩ ከታክስ ባለስልጣኑ ዘንድ ቀርበው ማወራረድ አለባቸው።

፪/ በወጭ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ላኪዎች ጫቱን ወደ ውጭ ያልላኩ ከሆነ ታክሱንና የታክሱን ፳፭በመቶ በመቀጫ መልክ የመክፈል ግዴታ አለባቸው።

፫/ የታክስ ባለስልጣኑ የዚህን አንቀጽ ዝርዝር አፈፃፀም የሚወስን መመሪያ ያወጣል።

፰. **ሌሎች ግብርና ታክሶችን የመክፈል ኃላፊነት**

ማንኛውም በጫት ንግድ ሥራ ላይ የተሠማራ ግብር ከፋይ በዚህ አዋጅ ከተጣለው የኤክሳይዝ ታክስ በተጨማሪ ፀንተው በሚሠራባቸው ሕጎች መሠረት ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን የመክፈል ኃላፊነት አለበት።

፱. **የኤክሳይዝ አዋጅ ተፈጻሚነት**

በዚህ አዋጅ ባልተደነገጉ ጉዳዮች ላይ የኤክሳይዝ አዋጅ ቁጥር ፫፻፯/፲፱፻፺፬ (እንደተሻሻለ) ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

፲. **የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

፩/ የጫት ግብርን ለማስከፈል የወጣው አዋጅ ቁጥር ፫፻፱/፲፱፻፹፱ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

፲፩. **የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

የጫት ግብርን ለማስከፈል በወጣው አዋጅ መሠረት መከፈል ሲገባው ይህ አዋጅ በሥራ ላይ እስከዋለበት ቀን ድረስ ያልተከፈለ ታክስ በዚያው አዋጅ መሠረት ገቢ እንዲሆን ይደረጋል።

b) shall give to the officer of the Tax Authority assigned at the place of collection of the tax , a voucher on which an amount proportional to the tax to be paid is entered when such exporters transport within Ethiopia the chat to be supplied to a foreign market;

c) shall export the chat and appear before the Tax Authority to settle the voucher on a monthly basis.

2/ The exporters of chat shall be liable to pay the tax and 25% of the tax as penalty if they fail to export the chat.

3/ The specific application of the provisions of this Article shall be prescribed by directive to be issued by the Tax Authority.

8. **Duty to Pay Other Taxes**

A tax payer liable to pay the tax levied under this Proclamation shall, in addition to excise tax, pay other direct and indirect taxes as determined by other applicable laws.

9. **Applicability of the Excise Tax Proclamation**

The Excise Tax Proclamation No. 307/2002 (as amended ) shall apply in respect of matters not provided for in this Proclamation.

10. **Repealed and Inapplicable Laws**

1/ The Chat Tax Proclamation No.309/1987 is hereby repealed.

2/ No law or customary practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable in respect to matters provided for in this Proclamation.

11. **Transitory Provision**

Tax payable under the Chat Tax Proclamation but unpaid until the effective date of this Proclamation shall be collected pursuant to the said Proclamation.

**፲፪. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፩ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም**

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**12. Power to Issue Regulation and Directive**

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued under sub-article (1) of this Article.

**13. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 27th day of August, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**